# <u>ውታፍ ነቃይ</u>

ከጣሰው እንደልቡ

ለዚህ ጽሁፌ ማሳሰቢያ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ ይሄውም ለመረጃዬ በጽሁፌ ውስጥ መረጃዎችን ተንተርሼ "ጋላ" እና "ኦሮሞ" የሚለውን የነገዱን ስም እያቀያዬርሁ ተጠቅሜአለሁ፡፡ ከዚህም ተጨማሪ 1ኛ - ክቡር አቶ ይልማ ደረሳም "የ16 ክፍለ ዘመን ታሪክ" በሚሉት መጽሀፋቸው፣ 2ኛ- አሁን በህይወት ያሉ የኦሮሞ ብሄረተኛ መሪዎች ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት ባስገቡት አቤቱታ ላይ ጋላ ሲሉ በመጻፋቸው፣ 3ኛ- አባ ዱላ ገመዳም "የኦሮሞ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት" በሚለው መጽሀፋቸው "ጋላ" ሲሉ መጥቀሳቸው እና በሌሎችም መረጃዎች፣ የታሪክ ጸሀፊው ጋላ ብሎ የጻፈውን የነገዱን ስም ኦሮሞ ብሎ ማቅረብ አግባብ ካለመሆኑም በተጨማሪ ህዝብን መዋሸትና ማደናገር ይሆናል በማለት ጋላ የሚለውን የነገድ ስም እንደመረጃው ተጠቅሜአለሁ፡፡ ጋላ ማለት ስድብ ነው የሚሉ ካሉ በምን መልኩ ስድብ መሆኑን ቢሞግቱኝ ለመማር ፈቃደኛ ነኝ፡፡

ወደ ጀመርሁት ርእስ ስገባ፣ የትግራይ ብሄረተኞች በአማራና በአፋር ክልል በከፈቱት ጦርነት ስለፈጸሙት ዘግናኝ ጭካኔና ጭፍጨፋ አስመልክቶ ሊቀ ጳጳሰ አቡነ ኤርሚያስ በአንድ ቃላ መጠዬቃቸው ላይ "ለምን" ብዬ እራሴን ለመጠዬቅ ተገደድሁ ይላሉ፡፡ አዎ! ማንም ህሌና ያለው ሰው "ለምን" ብሎ ለመጠዬቅ ይገደዳል፡፡ ዛሬ ውታፍ ነቃይ ብለን የምንነቅፋቸው ዜጎች "ለምን" ብለው መጠዬቅ አለመቻላቸውን ስናይ ነው፡፡

በወለጋ ተባብሶ አሁን ደግሞ ወደ ሰሜን ሸዋ የዞረው፣ የመንግስት ይሁንታ ያለው የሚመስለው ብሄርና ሃይማኖት ተኮር ጭፍጨፋን "ለምን" ብለን እንድንጠይቅ እንገደዳለን፡፡ ለምን ብለን በጠዬቅን ቁጥር ደግሞ ወደኋላ ሄደን ታሪክን መመርመር ግዴታ ይሆናል፡፡ ለዚህም ታማኝና በጽሁፍ ያሉ መረጃዎችን ስናገላብጥ መነሻም ሆነ መድረሻ የሚሆነን መጽሀፍ፣ በጊዜው የአይን ምስክር የነበሩት አባ ባህሪ በ1600 ክፍለ ዘመን በጋሞ አውራጃ የዝርዝር ማሪያም ገዳም መነኩሴ፣ በአራቱ ነገስታት፣ በንብለ ድንግል፣ በገላውዲዎስ፣ በሚናስና በሰርጸድንግል ዘመነ መንግስት በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን የጋላ ወረራ ችግር በአይናቸው ያዩና የችግሩ ተካፋይ የሆኑ "ዜናሁ ለጋላ" ሲሉ በግእዝ የጻፉትን መጽሀፍ፣ ቀደም ሲል መርስኤ ሀዘን ወልደቂርቆስ በኋላ ደግሞ ፕሮፌሰር ጌታቸው ሃይሌ ከግእዙ ወደ አማረኛ ተርጉመው ያስቀመጡልን የታሪክ መጽሀፍ ይሆናል፡፡

በመርስኤ ሀዘን ወልደጊዮርጊስ ትርጉም ላይ "እኒያ ከቦረና ተለይተው የቀሩት ከሀገራቸው በፋራ መንገድ ወጡ፣ ፋሲልም ዘመተባቸው ገደሉትም፣ ያን ጊዜም ዳቂ ክርስቲያንን መውጋት ጀመረ፣ ያን ጊዜ የዚህ ታሪክ ጸሀፊ (አባ ባህሪን ማለታቸው ነው) "የፋሲልን ገዳይ እፈራዋለሁ፣ የክርስቲያንን ደም ቀምሷልና" ሲል ትንቢት ተናገረ፡፡ እሱም ዳዌ በጥረ አሞራንና ወጂን አጠፋው፣ እንደ ቃሉም ሆነ፣ ዳዌ አባ ባህሪን አባረረው፣ ገሞ የተባለ ሀገሩንም አጠፋው፡፡ ዳዌ ገሞን ካጠፋው በኋላ፣ መከራ የከበደው ክርስቲያኑ ህዝብ ነፍሱን ለማዳን ሲል የወገኑ ሀይል ወደአለበት ወደ አማራው ሀገር ሲሸሽ አባ ባህሪም አብሮ ሸሽቶ በአማራ ሀገር የሚኖር ሆኖዋል፡፡" ይላሉ፡፡

ዛሬ ከወለጋ ጭፍጨፋ ሸሽተው ወደ አማራ ክልል የሚገቡት የአማራ ተወላጆችና የኢትዮጵያ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ሲናገሩ (ማንም ሰው በመረጃ ቲቪ ድህረገጽና በሶሺያል ሜዲያዎች እንደሚያዬው) ምንም ከፖለቲካው ጋር ግንኙነት የሌላቸው፣ ከመታረድ በእግዚአብሄር ቸርነት አምልጠው የመጡ ዜጎች፣ ኦነግ ሸኔዎች ሰውን ካረዱ በኋላ የሰው ደም እንደሚጠጡ ሲናገሩ በድምጽ ሰምተናል፣ በምስልም አይተናል፡፡ ይሄንን ቃለ መጠይቅ የሰማ ሰው አባ ባህሪ "የክርስቲያንን ደም ቀምሰዋልና

እፈራቸዋለሁ" ያሉትን በቀድሞ ግንዛቤው ገለዋል የሚለውን ቃል ትቶ በጥሬ ቃሉ የሰው ደም ጠጥተዋል የሚል ግንዛቤ ቢይዝ ስህተት አይሆንም፡፡

በበኩሌ ቀደም ሲል እንደማነኛው ሰው ከተፈናቃይ ዜጎች የተቀዱ ዘግናኝ ቃለ መጠይቆችን አዳምጨአለሁ፡፡ በተቻለኝም የጋላ ወረራን ታሪክ በተመለከተ ለማንበብ ሞክሬአለሁ፡፡ ይሁን እንጂ የማረድ፣ የማፈናቀሉና ደም የመጠጣቱ ነገርን "ለምን" ብዬ ለራሴ ለማቀርበው ጥያቄ አሳማኝ መልስ ላገኝለት አልቻልሁም፡፡

ለትዳር የደረሱ ልጅአገረዶችን ከማረዳቸው በፊት በብልታቸው እንጨት ከተው ያሰቃዩዋቸዋል፣ ብሄርና ሃይማኖት ተኮር ግድያ በገፍ ይፈጽማሉ፣ እርጉዝ ሴትን ሆዷን ቀደው ሽሉን ካወጡ በኋላ ይገሏታል፣ እና ሌሎችንም ዘግናኝ ጭካኔዎችን ይፈጽማሉ፡፡ ይሄ ሁሉ አረመኔነት ለምን፡፡ ከወራት በፊት አቶ ሌንጮ ለታ ከቤተልሄም ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቃቸው እንደተረዳሁት "የኦሮሞን ህዝብ አንድነት ለመፍጠር" መሆኑን በገደምዳሜም ቢሆን ነግረውናል፡፡

ይህ ሁሉ ጭካኔና ጭፍጨፋ የኦሮሞን ህዝብ ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ነጥሎ፣ አጋጭቶና አቃቅሮ የተለዬና ወደ እራሱ ብቻ የሚመለከት ህዝብና ኦሮሚያ የሚባል ሀገር ለመፍጠር ከሆነ በአሸዋ ላይ የተገነባ ቤት ከመሆን አያልፍም፡፡

ታሪክ እንደሚያስረዳን ከሆነ፣ ዛሬ ኦሮሞኛ የሚናገረው ህዝብ ትናት ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ የነበረና ተገዶ ኦሮሞኛ እንዲናገር ሆኖ፣ ማንነቱን የቀየረ ህዝብ ለመሆኑ ሌላው ቀርቶ የኦሮሞ ህዝብ ባለ ውለታ ብለው እነ አብይ አህመድ አሊ የሸለሙት መሀመድ ሀሰን (ለመጽሀፍ ጥቆማው አቶ አቻምየለህ ታምሩን እያመሰገንሁ) ገዳ ብሎ ለዶክትሬቱ መመረቂያ በጻፈው ስራው ይመሰክራል፡፡ ዛሬ የአሩሲ ኦሮሞ የሚባለው ሁለት ሶስተኛው ህዝብ ተገዶ ማንነቱን የቀዬረ የሀድያ፣ የጉራጊ፣ ያማራና የሌሎች ነገዶች ህዝብ ነው፡፡ የደጃዝማች ኩምሳ ወረዳን ታሪክ የሚተርከው የሜጫ የዘር ሀረግ የያዘው የወለጋ ነገስታት ታሪክ መጽሀፍ የሚያስነብበን ዘጠኝ እጁ ገርባ ወይም ከሌላ ብሄር ሲሆን፣ አንድ እጁ ብቻ ኦሮሞ መሆኑን ይገልጻል፡፡ ይህ ማለት ዛሬ ኦሮሞ ነኝ ብሎ ከሚያቅራራው ከአስሩ አንዱ ብቻ ኦሮሞ መሆኑን ነው፡፡ ሀረር፣ ወለጋ፣ አሩሲ ያሉ የዛሬ ኦሮሞኛ ተናጋሪዎች ኦሮሞዎች ሳይሆኑ ቋንቋቸውን የቀየሩ ናቸው፡፡ እኛን መስላችሁ፣ የእኛን አባት ተቀብላችሁ መኖር ትችላላችሁ ተብለው ተገደው የሞጋሳ ልጅ የሆኑ ናቸው፣ ኦሮሞ ያልሆነው ነባሩ ህዝብ ከመገደል ለመዳን ሲል የሞጋሳ ልጅ ሆኖዋል፡፡ የሀገር ውስጥ ታሪክ ጸሀፊዎችም ሆኑ የውጭ ሀገር ታሪክ ጸሀፊዎች እነ አሎንዶልፍ፣ ጀምስብሩስ፣ ሀንቲንግ ፎርስ ወይም ሌሎቹ የሚተርኩልን ይሄንን ሀቅ ነው፡፡

የኦሮሞ ብረተኞች ሰከን ብለው ማሰብ ያለባቸው ጊዜ ይመስለኛል፡፡ የዛሬው ትውልድ እንደ 1960ዎቹ ካፒታልን ሳያነብ ከርል ማርክስ እንዳለው እያለ የሚኮፈስ አስመሳይ ትውልድ አለመሆኑን ማወቅ አዋቂነት ነው፡፡ ከውታፍ ነቃዮች በቀር ሌላው ህሌና ያለው ሰው ሁሉ "ለምን" ብሎ መጠዬቅ፣ ማንበብና መመርመር ከጀመረ፣ የአለፈ ታሪካችን የሚነግረን ወደ አስከፊ መለያዬትና መጋደል እንጂ የሚያቀራርብ ሆኖ አይታዬኝም፡፡

አማሮች ኦሮሚያ ክልል በሚባለው በተለይ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ አሊ ስልጣን ላይ ከመጣ ጊዜ ጀምሮ በአሰቃቂ ሁኔታ እየተገደሉ ናቸው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ አሊ ባሌ ላይ እንደተናገረው ኦሮሞ ዝሆን ሆኖ የሚጨፈልቅ ከሆነ፣ እንደ ሽመልስ አብዲሳ የመስቀል አደባባይ ንግግር "እንሰብራችኋለን" ከሆነ፣ "አንሰበርም!!፣ አንጨፈለቅም!!" የሚል ህዝብ እራሱን ለመከላከል ሲል ይነሳል፡፡ የኦሮሞ ብሄረተኞች እንደሚያስቡት ሳይሆን በተቃራኒው የኦሮሞን ህዝብ አንድነትና ሰላም የሚንድ መንገድ እየተከተሉ ነው፡፡ ነፍሳቸውን ይማርና አቶ አሰፋ ጫቦ አንድ ጊዜ እንዳሉት፣

ከቀድሞ ትዝታው ያልተላቀቀን ህዝብ በሰላምና በፍቅር ካልያዝከው ነገ ፊቱን በቂም በቀል ወደ ኦሮሞ ህዝብ የሚያዞር ይሆናል፡፡

ከኦሮሞ ክልል የተፈናቀሉት ወገኖች የትጥቅ፣ የመሳሪያ ያለህ እያሉ ነው፡፡ በያዝነው ሳምንት ውስጥ ኗሪነታቸው አሜሪካ የሆነ ወለጋ ተወልደው ያደጉ አማራዎች በወላጆቻቸው ላይ የሚፈጸመውን ጭፍጨፋ አውግዘው መግለጫ አውጥተዋል፡፡ በጥር 25 መሰለኝ ኢሰመጉ ባወጣው ራፖርት - የከረዩ አባ ገዳዎችን በመንግስት የጸጥታ ሀይሎች ተገለዋል፡፡ ሁኔታዎች የሚያሳዩት እንደፈጥጣችኋለን፣ እንሰብራችኋለን የተባሉት ወደ አንድነት እየመጡ፣ ደፍጣጮችና ሰባሪዎች ከአንድነት ይልቅ ወደ መለያዬትና መበታተን መሄዳቸውን ነው፡፡ ይህ ደግሞ እዚያው ኦሮሚያ ክልል ውስጥ የእርስ በርስ መተላለቅ እንደሚአስከትል ጠቋሚ ነው፡፡ ምንም እንኳ በኦሮሞዎች መካከል እርስ በርስ የመገዳደል ታሪክ አዲስ ክስተት ባይሆንም፡፡  ዛሬ የሚረግሟቸው አፄ ሚኒሊክ መጥተው እስኪያስቆሙት ድረስ፣ አባ ገዳዎች በገዳ ስርአታቸው ገባርና አዲስ መሬት ፍለጋ እርስ በእርስ ይተላለቁ እንደነበር የታሪክ ማስረጃዎችን ማቅረብ ቀላል ነው፡፡

በየ 8 ዓመቱ አንዱ ሉባ ለሌላ ሉባ ስልጣኑን በሚለቅበት ጊዜ ዘመቻ ይደረጋል፣ ይህ ዘመቻ ቀዳሚው ሉባ ያልወጋውን ሀገር በመውጋትና በመዝረፍ ነበር፡፡ ይሄን ዘመቻ በሚያደርጉበት ጊዜ ህጻን - ሽማግሌ፣ ሴት - ወንድ፣ ወታደር ወይም ሲቪል ብለው ሳይመርጡ ያገኙትን ሰው ሁሉ መግደል ነበር፡፡ አንድ ሉባ ስልጣኑን የሚያገኘው በገደለው ሰው ብዛት የበላይነት ያገኘው ነው፡፡ በዚህ አይነት የመግደል ዘመቻ 28 ያህል ነገዶች ከሀገራችን ጠፍተዋል፡፡ የጭፍጨፋው አይነት ሲታይ ዛሬ በመንግስት ይሁንታ ያለው ከሚመስለው የኦነግ ሸኔ ጭፍጨፋ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ይህ አይነት ጭፍጨፋና ጭፍጨፋውን ተተከትሎ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ የኦሮሞ ብሄረተኞች ሰከን ብለው ሊያስቡበት ይገባል፡፡

መንግስት የህዝብን አብሮ የመኖርና ሰላም የማስጠበቅ ሀላፊነቱንና ስልጣኑን ተጠቅሞ ሲሆን ማስቆም፣ ካልሆነም መከላከል ሲገባው፣ ለጭፍጨፋው ትኩረት እንኳ አለመስጠቱ ሲታይ፣ ጠቅላይ ሚኒስቴር አብይ አህመድ አሊ ሀገራችንን ወደ እርስ በርስ ጦርነት እየከተታት ነው የሚለው ስጋት የብዙዎቹ ሆኖዋል፡፡

ኢትዮጵያዊነታቸው ጥያቄ ውስጥ የማያስገቡ ከኦሮሞው ነገድ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ሀፍረትና መሸማቀቅ ውስጥ እንዲገቡ እዬተደረገ ነው፡፡ ሀገርን ከውጭ ወራሪ፣ ከውስጥ ሰላምንና አንድነትን አስጠብቀው ለሀገራቸው ብዙ የሰሩ ኩሩ የኦሮሞ ተወላጆችን ከቀሪው የኢትዮጵያ ህዝብ ለመነጠልና የነአብይን የኦሮሙማ ሀገር ለመፍጠር የሚደረግን ተንኮልና ሴራ የሚጠየፉ እንደ ታምራት ነገራ አይነት የኦሮሞ ተወላጆች በሺዎች አልፎም በሚሊዮኖች ወደ አደባባይ የሚወጡበት ቀን እሩቅ አይሆንም፡፡ ማንም ኩሩ የኦሮሞ ተወላጅ ዛሬ በኦሮሞ ስም ሃይማኖትና ብሄር ተኮር ጭፍጨፋን የሚቀበል ህሌና አይኖረውም፡፡

ወያኔ ስልጣን እንደያዘ ጦቢያ የሚል መጽሄት ይወጣ ነበር፣ ታዲያ አንዱ የወያኔዎችን የብሄር ፖለቲካ አስመልክቶ "የጫሩት አሳት መልሶ እራስን ይለበልባል" ሲል ለጻፈው ጽሁፍ ወያኔዎች የመለሱለት "ከተረት ያለፈ አታውቁም" የሚል ነበር፡፡ ይሄው ዛሬ ብሄረተኝነቱ የትግራይን ህዝብ ምን ያህል እንደጎዳው አይቶ መማር ሲገባ፣ እነ አብይ አህመድ አሊ ግን ከወያኔም በከፋ መልኩ እያስተናገዱት ይገኛሉ፡፡ "ለሀጢያተኞች የተወረወረ ለጻድቃን ይተርፋል" እንደሚባለው፣ ኦሮሞኛ ተናጋሪ ወንድሞቻችን በነአብይ አህመድ እንጨፈልቃለን የሚል ነውረኝነትና ትእቢት በፈጠረው የፖለቲካዊ ቁማር እየተሸማቀቁ ናቸው፡፡